# የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን

## አገር በቀል የግል ኦፕሬተሮች
## የፋይናንስ
## አፈጻጸም መመሪያ

658/2013

ኢ.ሲ.አ.ባ.

ጥቅምት 2012

አዲስ አበባ

**ማውጫ**

**ርዕስ** **ገጽ**

1. **መግቢያ** -------------------------------------------------------------------------------------1
2. **የግል ኦፐሬተሮች የፋይናንስ አፈጻጸም መመሪያ**----------------------------------------3
3. **የግል ኦፐሬተሮች በኢትዮጵያ**-------------------------------------------------------------9
4. **የግል ኦፐሬተሮች ያሉበት ነባራዊ ሁኔታ**------------------------------------------------11
5. **የግል የአየር ኦፐሬተሮች ኢኮኖሚያዊ አስተዋጾኦ**--------------------------------------14
6. የአየር ትራንስፖርት የኢኮኖሚ ሬጉሌሽን **በፋይናንስ እይታ**---------------------------16
7. የአየር ኦፐሬተሮች የኢኮኖሚ ቁጥጥር አግባቦች ተሞክሮ-------------------------------17
8. **ተያያዥ ቅጾች**-----------------------------------------------------------------------------19

# I. መግቢያ

ከ15 ዓመታት ወዲህ መንግስት የግል ባለኃብቱ በተለያዩ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ኢንቨስት እንዲያደርግ በማሰብ የአገሪቱን የኢኮኖሚ ልማት በማፋጠን፣ የህዝቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል በማሰብ የአቪዬሽን ኢንዱስትሪውም ትኩረት እንዲያገኝ ተደርጓል፡፡

በዚሁ መሰረት የጠቅላላ የአቪዬሽን አገልግሎት የኢንዱስትሪው አካል አንዱ በመሆኑ፣ ዘርፉ እንዲስፋፋ በማድረግ፣ ጤናማ የሆነ ተወዳዳሪነትን በማስፈን ተጠቃሚው የተለያዩ አማራጮች እንዲኖረው እንዲሁም ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዲኖረው በማሰብ በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 ከ50 መቀመጫዎች ያልበለጡ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን ባለሃብቶች በንግድ ሥራው እንዲሳተፉ በአዋጅ ተፈቀደ፡፡

የአዋጁን መውጣት ተከትሎ ከ30 በላይ የግል ባለኃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ አውጥተው መንቀሳቀስ ጀምረው ነበር፡፡ ሆኖም ግን ካንፓኒውን ለማቋቋም እንዲሁም የንግድ ሥራው ለማስኬድ ከፍተኛ የካፒታል ወጪ (the high capital costs of establishing and running airlines) ስለሚጠይቅ፣ ለዘረፍ በልዩ ሁኔታ የሰለጠነ የሰው ኃይል ገብያ ላይ በስፋት ለማግኘት አዳጋች በመሆኑ እና በሌሎች በራሳቸው ምክንያት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከወሰዱት ውስጥ ተመናምነው በአሁኑ ወቅት እስከ 8 የሚደርሱ ኦፐሬተሮች ይገኛሉ፡፡ እነዚህም አቢሲኒያ የበረራ አገልግሎት፣ትራንስ ኔሽን ኤይርዌይስ፣ አኳሪየስ አቪዬሽን፣ ናሽናል ኤይርዌይስ፣ ዘመን የበረራ አገልግሎት፣ኢስት አፍሪካ አቪዬሽን፣ ዋሊያ ኤርዌይስ፣ አሚባራ የእርሻ ልማት ድርጅት ኦፐሬተሮች በአብዛኛው የቻርተር ፣ የአንቡላንስ ፣ የጭነት እና የርጭት አገልግሎት መደበኛ ያልሆኑ በረራዎች በሀገር ውስጥ እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት በዘርፉ ለማሰማራት የኢንቨስትመንት ፈቃድ በመውሰድ ወደ ቢዝነስ ስራ ለመግባት እንቅስቃሴ እያደረጉ ያሉ አዳዲስ ባለሃብቶችም ይገኛሉ፡፡

ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ በአዋጅ ከተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች አንዱና ዋናው ውስጥ የአቪዬሽን እንዱስትሪው በአገሪቱ እንዲስፋፋ ማድረግ ሲሆን በተለይ የግል ዘርፉ በአየር አገልግሎትና ለጠቅላላ የአቪዬሽን አገልግሎት ለመሳተፍ የስራ ፈቃድ ከመስጠት ባሻገር ተያያዥ መመሪያዎችን በማዘጋጀት እና ቁጥጥር በማድረግ የግል የአቪዬሽን ዘርፉ የተፈለገው እድገት እንዲያስመዘግቡ መርዳት ይጠበቅበታል፡፡ ከዚሁ በተጨማሪ በተለይ በግል ኦፐሬተሮች ተዘውትረው የሚነሱ ለሥራዎቻቸው እንቅፋት የሆኑ ችግሮች በመለየት ለዘርፉ እድገት አፋጣኝ የሆኑ የመፍትሄ አቅጣጫዎች ማስቀመጥ ይጠበቅበታል፡፡

የግል ኦፐሬተሮች መስፈርቱ በሚጠይቀው አሟልተው የኢንቨስትመንት ፈቃድ አውጥተው አስፈላጊው ማበረታቻ (Incentives) ተደርጎላቸው ፣ ንግድ ፈቃድ እና የአየር ኦፐሬተር ሰርተፍኬት ወስደው ወደ ንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ከገቡ በኋላ በሀገር ውስጥ፣ በአጎራባች እና በሌሎች ሀገራት የሚሰጧቸው የበረራ አገልግሎት ግልጽነት የተላበሰ እንዲሆን፣ ከገልግሎቱ ለዜጎች በተፈለገው መጠን የስራ እድል በመፍጠር እንዲቻል እንዲሁም ከተገኘው ገቢ እና ከውጭ ምንዛሪ ግኝት ለመንግስት ተጠቃሚ እንዲሆን ለማስቻል ፣የፋይናንስ መመሪያው ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ይህ የፋይናንስ መመሪያ ትኩረት የሚያደርግባቸው በዋናነት የግል ኦፕሬተሮች ወቅታዊ የአየር ትራንስፖርት እስታትስቲክስ የተሳፋሪ፣ የጭነት አገልግሎት፣ የስልጠና እና ተያያዥ መረጃዎች እንዲያቀርቡ፣ የፋይናንስ አቋም መረጃዎች ማለትም ወቅታዊ የገቢና የወጭ መረጃዎች ፣ በውጪ የሚደረጉ ኦፕሬሽኖች (በረራዎች) የፋይናንስ ዝውውር መረጃ እና የባንክ ማረጋገጫ የሂሳብ መግለጫዎች እንዲሁመ ኦፕሬተሮች የአውሮፕላን ኪራይና ግዥ ሲፈጽሙ የገንዘብ ዝውውር ሁኔታ ሰነድ የያዙ መረጃዎች የተመለከቱ ጉዳዮች ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በየወቅቱ ማሳወቅ እንዳለባቸው ትኩረትን በማድረግ የተዘጋጀ የፋይናንስ አፈጻጸም መመሪያ ነው፡፡

በመጨረሻም መመሪያው በአባሪነት የግል ኦፕሬተሮች በኢትዮጵያ ያሉበት ሁኔታ ፣የግል ኦፕሬተሮች አገራዊ እና አለማቀፋዊ ነባራዊ ሁኔታ፣ የግል የአየር ኦፕሬተሮች ኢኮኖሚያዊ አስተዋጾኦ፣ የአየር ትራንስፖርት የኢኮኖሚ ሬጉሌሽን በፋይናንስ እይታ፣ የኦፕሬተሮች የኢኮኖሚ ቁጥጥር አግባቦች ተሞክሮ በመጨረሻም የሚፈለጉት መረጃዎች ለማሰባሰብ የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ቅጾች አካቶ እንዲይዝ ተደርጓል፡፡

# የሀገር በቀል የግል ኦፕሬተሮች የፋይናንስ አፈጻጸም መመሪያ

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አውጪው ባለሥልጣን

የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 616/2001 አንቀጽ 92(2) መሰረት መመሪያን በማውጣት በአዋጁ ላይ የተዘረዘሩት ተግብርና ኃላፊነቶች ስርዓቶችና ደረጃዎች የያዙ ተከታታይነት ያለው የኢኮኖሚ ቁጥጥር ለማድረግ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት ይህን መመሪያ አውጡቷል፡፡

### 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ " አገር በቀል የግል ኦፕሬተሮች የፋይናንስ አፈጻጸም መመሪያ 658/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 3. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉ ቃላትና ሃረጎች የሚከተለውን ትርጉም ይይዛሉ ፤

ሀ. ***የግል ኦፕሬተር*** ፡ ማለት በኢትዬጵያ ምዝገባ በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር ፈቃድ አግኝተው የሚሰሩ እንዲሁም በውጭ አገር ምዝገባ ***ኢትዮጵያ ውስጥ*** የቻርተር፣ የመደበኛ፣ የውጭ ንግድ ለራሱ ጥቅም በክፍያ ወይም በኪራይ የአየር አገልግሎት የሚሰጥ የአየር አጓጓዥ ማለት ነው፡፡

ለ. ***የኪራይ ውል*** ፡ ማለት ለአጭር ወይም ለረጅም ጊዜ የአውሮፕላን አከራይ እና ተከራይ ወገኖች የሚደረግ የአውሮፕላን ኪራይ ስምምነት ነው፡፡

ሐ. ***የኪራይ ዓይነት፡*** ማለት ለአጭር ጊዜ እና ለረጅም ጊዜ በአከራይና በተካራይ ስምምነት የሚደረግ የጊዜ ገደብ ማለት ነው፡፡

መ. ***ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን*** ፡ ማለት የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን ማለት ነው

ሠ. ***"መመሪያ"*** ማለት አገር በቀል የግል ኦፕሬተሮች የፋይናንስ አፈጻጸም መመሪያ "

ቁጥር------ማለት ነው፡፡

### 4. የመመሪያው የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ክልል እና በወጭ ሀገራት የአየር አገልግሎት ለመስጠት በኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን ተመዝግበው ወይም ፈቃድ አግኝተው በተቋቋሙ የግል ኦፕሬተሮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 5. የመመሪያው ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ የግል ኦፕሬተሮች :-

ሀ. መስፈርቱ በሚጠይቀው ሁኔታ አሟልተው የኢንቨስትመንት ፈቃድ አውጥተው አስፈላጊው ማበረታቻ (Incentives) ተደርጎላቸው፣ ንግድ ፈቃድ እና የአየር ኦፕሬተር ሠርተፍኬት አውጥተው ወደ ንግድ ሥራው ከገቡ በኋላ የሚሰጧቸው የበረራ አገልግሎት ግልጽነት የተከተለ እንዲሆን፤ ኦፕሬተሮቹ በሚሰጧቸው አገልግሎቶች ለዜጎች የስራ እድል በመፍጠር፣ ከተገኘው ገቢ እና ከውጭ ምንዛሪ ለመንግስት ገቢ በማስገኘት የራሳቸው ሚና እንዲጫወቱ ለማስቻል፣

ለ. የግል ኦፕሬተሮች በተዘረጋው አሰራር ሥርዓት ተፈላጊ መረጃዎች በተሟላ መልኩ ለባለሥልጣኑ በወቅቱ እንዲያቀርቡ በማድረግ የፋይናንስ ግልጽኝነትና ተጠያቂነት ለማረጋገጥ፣

ሐ. ወቅተዊ የሆኑ መረጃዎችን በመዳሰስ የግል ኦፕሬተሮች በሰለጠነ የሰው ኃይል፣የፋይናንስ አቅም ተያያዥ ሁኔታዎች በመዳሰስ የቢዝነስስ ስራው ለመምራት በሚያስችል ቁመና (Status) ላይ ስለመሆናቸው ለመገምገም እና አስፈላጊው የመፍትሄ አቅጣጫ ለማስቀመጥ ነው፡፡

## 6. መርሆዎች

ኦፕሬተሮች በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ሲያከናውኑ የሚከተለትን መርሆዎች መሠረት ማድረግ አለባቸው ፡፡

ሀ. የግል ኦፕሬተሮች በባለሥልጣኑ የሚጠየቅ መረጃዎች ግልጽ እና ወቅቱን ጠብቀው ማቅረብ እንዳለባቸው ይህ ባይሆን ግን ተጠያቂነት የሚያስከትል መሆኑን መረዳት አለባቸው፣

ለ. ባለሥልጣኑ ከግል ኦፕሬተሮች መረጃዎች ከሰበሰበ በኋላ ተሟልቶና ወቅቱን ጠብቆ በማጠናቀር ለሚመለከተው አካል ተደራሽ ማድረጉን ማረጋገጥ፣

# ክፍል ሁለት
# የግል ኦፕሬተሮች መፈጸም ያለባቸው ተግባርና ኃላፊነቶች

## 7. የአየር ትራንስፖርት ስታትስቲካዊ መረጃ ማቅረብ፣

አንድ የግል ኦፕሬተር በአገር ውስጥ እና በውጭ በሚደረጉ በረራዎች በተመለከተ እና ተያያዥ መረጃዎች በመሰብሰብ፣ በማደራጀት እና በመተንተን በማቅረብ ከሴፊቲ፣ ከአከባቢ ብክለት ለመከላከል፣ ቀጣይነት ያለው የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጡ ለማስቻል ባለሥልጣኑ የቀረበለትን የስታትስቲካል መረጃዎች በመመዝገብ ፣ በማደራጀት እና በመተንተን ከሌሎች መሰል መረጃዎች ጋር በማደራጀት ዓመታዊ ስታትስቲካል መጽሄት እንዲታተም ያደርጋል፡፡ በዚህ መሰረት አንድ የግል ኦፕሬተር የሚከተሉት ወቅታዊ የስታትስቲካል መረጃዎች ማቅረብ ይጠበቅበታል፤

ሀ. በአየር አገልግሎት የተሰማራ አገር በቀል የግል ኦፕሬተር  የሚከተሉት ወቅታዊ የሆኑ መረጃዎች ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፤

- የመንገደኛ ፣
- የጭነትና የፖስታ፣
- የአውሮፕላን እንቅስቃሴ (aircraft movements)፣
- የአውሮፕላኑ ዓይነት፣ አገልግሎት እና ብዛት፣
- አውሮፕላኑ የተገኘበት  ሁኔታ (የተገዛ፣ በኪራይ ፣ የኪራይ ግዥ)፣
- አውሮፕላኑ የተመረተበት ዓ/ም
- ኦፕሬተሩ /ድርጅቱ ያለው ሰው ኃይል ስብጥር፣

ለ. የሚሰጡት የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት የተመለከቱ ስታትስቲካል መረጃዎች ለባለሥልጣኑ በሚላክለት ፎርም መሰረት ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

ሐ. የግል ኦፕሬተሩ የሰበሰበው ስታትስቲካል መረጃዎች አገልግሎቱን ከሰጠ ከሶስት ወራት በኋላ ለባለሥልጣኑ በ10 ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

መ. ከላይ በተገለጸው ጊዜ ገደብ ውስጥ መረጃወን አሟልቶ የማያቅረብ ኦፕሬተር እንደ ጥፋቱ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ይደርሰዋል፡፡

ሠ. ለሁለተኛ ጊዜ ያላቀረበ ኦፕሬተር ማንኛውም አገልግሎት እንዳያገኝ ይደረጋል፡፡

**8. የፋይናንስ አቋም መረጃ (ወቅታዊ የገቢ፣የወጪ እና ተያያዥ መረጃዎች) ማቅረብ፣**

ማንኛውም በስራ ላይ ያለ የግል ኦፕሬተር የሚከተሉት መረጃዎች ለተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፡፡

ሀ. መደበኛ ላልሆነ(ቻርተር) በረራ አገልግሎት የገባውን የኮንትራት ውል ከበረራ ፈቃድ ጥያቄው ጋር አያይዞ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይጠበቅበታል፤

ለ. የየወሩ ጥቅል ገቢና የወጪ መረጃዎች ከመመሪያው ጋር ተያይዞ በቀረበው ቅጽ መሠረት  ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

ሐ. በውጭ አገር በተደረጉ የኦፕሬሽን ሥራዎች (የመንገደኛ ፣ የጭነት እና የጠቅላላ አቪዬሽን) ጋር በተያያዘ የተገኘ ገቢ እና የፋይናንስ ዝውውር (financial transaction) መሆኑን የሚያስረዳ የባንክ ማረጋገጫ  ሰነድ ማቅረብ ይኖርበታል፣

መ. አጠቃላይ የፋይናንስ አፈጻጸም የሚያሳይ የባንክ ማረጋገጫ ማስረጃ (Bank Statement of Transaction) ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

ሠ. አክሲዮን ወይም የሽርክና ማህበር መሠረት የሆነውን ካፒታል ለማሳደግ ወይም ለማሳነስ የተደረገ የውል ሰነድ ካለ በወቅቱ ማሳወቅ አለበት፣

ረ. ኦፕሬተሩ ከላይ በፊደል ተራ ሀ-ሐ የተገለጹት መረጃዎች በተሟላ ሁኔታ ለባለሥልጣኑ በየሩብ ዓመቱ መጨረሻ በ10 ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

ሰ. ከላይ በተገለጸው ጊዜ ገደብ ውስጥ መረጃወን አሟልቶ የማያቅረብ የግል ኦፕሬተር ለመጀመሪያ ጊዜ  በጽሁፍ  የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ይደርሰዋል፡፡

ሸ. ለሁለተኛ ጊዜ ያለቀረበ የግል ኦፕሬተር እስከብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ) የሚደርስ የገንዘብ ቅጣትና ማንኛውም አገልግሎት እንዳያገኝ ይደረጋል፡፡

## 9. የአውሮፕላን ግዥና ኪራይ አፈጻጸም መረጃ ማቅረብ

በባለሥልጣኑ የአውሮፕላኑ ብቃት ለማረጋገጥ የወጣው ደንብና ስታንዳርድ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ የግል ኦፕሬተር አውሮፕላን ሲገዛ፣ ሲከራይ ወይም ሲያከራይ ተዋዋይ ወገኖች አከራይና ተከራይ ወይም ሻጭና ገዢ የሚከተሉትን ግዴታዎች ማሟላት አለባቸው፡፡

ሀ. በአውሮፕላን ሊዝ ስምምነቱ (Aircraft Utlization Agreement) ሰነድ ውስጥ በዋናነት ፡-

- በስምምነቱ ሊገለጹ የሚችሉ ቃላት ትርጓሜዎች
- የአውሮፕላኑ ዓይነት እና የስሪት ቁጥር
- አውሮፕላኑ የተመዘገበበት አገር እና የተመዘገበበት መለያ ምልክት
- የአውሮፕላኑ የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት አሟልቶ የተሰጠው የአውሮፕላን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት የሚገልጽ አረፍተነገር
- የአውሮፕላኑ አከራይ ስም እና አድራሻ
- የአውሮፕላኑ የኪራይ ጊዜ ቆይታ
- የአውሮፕላኑ የኪራይ ዓይነት
- የሊዝ ስምምነቱ የሚጀምርበት ቀን
- የሊዝ ክፍያ ሁኔታ
- የአውሮፕላኑ ኦፕሬሽ ሁኔታ እና ለመጠገን የሚወሰዱ ኃላፊነቶች
- የኢንሹራንስ /የአውሮፕላን ቅያሪ
- በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች ያለመስማማት ሲከሰት የሚፈታበት ሁኔታ ያያዘ መረጃ ሰነድ ማቅረብ አለበት፡፡

ለ. አከራዩ ወይም ሻጩ ስለ አውሮፕላን ጥገና እና በስልጠና ማንዋሎች የተዘረዘሩት እንደአስፈላጊነቱ በሊዝ ስምምነቱ ውስጥ መካተት አለባቸው፣

ሐ. የሊዝ ወይም የግዥ ክፍያ ዝውውሩ የሚፈጸመው በካሽ መሆኑ ቀርቶ በባንክ የገንዘብ ዝውውር (Bank financial transaction) መሰረት መሆን አለበት፡፡

መ. የተጠናቀቀው የሊዝ ውሉ ስምምነት እና አስፈላጊው የባንክ ክፍያ ሰነዶች እንደተፈጸመ በ15 ቀናት ውስጥ ለተቆጣጣሪው ባለሥልጣን መቅረብ አለበት፡፡

ሠ. ይህንን ተግባራዊ ለማያደርግ የግል ኦፕሬተር ምንም ዓይነት የአውሮፕላን ምዝገባ (Registration) አይፈጸምለትም፡፡

ረ. ለሁለተኛ ጊዜ ተመሳሳይ ተግባር የፈጸመ የግል ኦፕሬተር እስከብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ) ብር የሚደርስ የገንዘብ ቅጣትና ማንኛውም አገልግሎት እንዳያገኝ ይደረጋል፡፡

## ክፍል ሶስት

## 10. መመሪያው ያለመፈጸም የሚያስከተለው ተጠያቂነት

ሀ. ይህ መመሪያ አለመፈጸሙ ሲረጋገጥ መመሪያውን እንዳይፈጸም ባደረገ ማንኛውም አካል አግባብ ባለው ህግ እና ተዛማጅ ደንቦችና መመሪያዎች እንደ ጥፋቱ ሁኔታ በህግ ተጠይቆ ቅጣት ሊወሰንበት ይችላል፡፡

**11. መመሪያውን ስለማሻሻል**

ሀ. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መመሪያው በባለሥልጣኑ ሊሻሻል ይችላል፡፡

**12. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ**

ሀ. ይህ መመሪያ ከ-----------ቀን 2012 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

# አባሪዎች

# Aircraft Data

## Abyssinian Flight Services

| No. | Aircraft Type | Reg. Mark | Role of Aircraft for | | Capacity (size) | Property Type | | | Years of production | Total No. |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | Passengers &Cargo | Training | | Owned (purchased) | Leased | | | |
| | | | | | | | WL | DL | | |
| 1. | C-208 | ET-ALD | √ | | 12 | | | √ | 1989 | |
| 2. | C-208 | ET-AQX | √ | | 12 | | | √ | 2014 | |
| 3. | C-208 | ET-AMV | √ | | 12 | | | √ | 2008 | |
| 4. | C-208 | ET-AMI | √ | | 12 | | | √ | 2007 | |
| 5. | C-208 | ET-AOF | √ | | 12 | | | √ | 2010 | |
| 6. | C-208 | ET-AUL | √ | | 12 | | | √ | 2016 | |
| 7. | C-208 | ET-AWD | √ | | 12 | | | √ | 2018 | |
| 8. | C-172S | ET-AQA | | ✓ | | √ | | | 2006 | |
| 9. | C-172R | ET-AQU | | ✓ | | √ | | | 1998 | |
| 10. | C-172S | ET-ASB | | ✓ | | √ | | | 2003 | |
| 11. | C-172S | ET-ASD | | ✓ | | √ | | | 2004 | |
| 12. | DA-42NG | ET-ASF | ✓ | | | √ | | | 2007 | |
| 13. | DA42NG | ET-APE | ✓ | | | √ | | | 2005 | |
| 14. | DA40NG | ET-APT | ✓ | | | √ | | | 2005 | |
| 15. | DA-40NG | ET-ATO | ✓ | | | √ | | | 2011 | |
| 16. | BELL H407 | ET-AUS | ✓ | | 6 | | | √ | 2009 | |
| **Total Sum** | | | **12** | **4** | | **8** | | **8** | | **16** |

## National Airways

| No. | Aircraft Type | Reg. Mark | Role of Aircraft for | | Capacity (size) | Property Type | | | Years of production | Total No. |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | Passengers & Cargo | Training | | Owned (purchased) | Leased | | | |
| | | | | | | | WL | DL | | |
| 1 | EMB-145 | ET-AUU | ✓ | | 50 | √ | | | 2000 | |
| 2 | EMB-145 | ET-AUY | ✓ | | 50 | √ | | | 2002 | |
| 3 | EMB-145 | ET-AUV | ✓ | | 50 | √ | | | 2001 | |
| 4 | EMB-145 | ET-AVV | ✓ | | 50 | | | √ | 2004 | |
| 5 | EMB-145 | ET-AVU | ✓ | | 50 | | | √ | 2004 | |
| **Total Sum** | | | **5** | | | **3** | | **2** | | **5** |

## Salini

| No. | Aircraft Type | Reg. Mark | Role of Aircraft for | | Capacity (size) | Property Type | | | Years of production | Total No. | Remark |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | Passengers & Cargo | Training | | Owned (purchased) | Leased | | | | |
| | | | | | | | WL | DL | | | |
| 1 | C-208 | ET-AMO | | | 12 | √ | | | 2008 | 1 | Company purpose |
| **Total Sum** | | | | | | 1 | | | | 1 | |

## Walya Airways

| No. | Aircraft Type | Reg. Mark | Role of Aircraft for | | Capacity (size) | Property Type | | | Years of production | Total No. |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | Passengers & Cargo | Training | | Owned (purchased) | Leased | | | |
| | | | | | | | WL | DL | | |
| 1 | EMB-145 | ET-AUT | ✓ | | 50 | | | √ | 2000 | |
| 2 | EMB-145 | ET-AVY | ✓ | | 50 | | | √ | 2000 | |
| **Total Sum** | | | **2** | | | | | **2** | | **2** |

## Aquarius Aviation PLC

| No. | Aircraft Type | Reg. Mark | Role of Aircraft for | | Capacity (size) | Property Type | | | Years of production | Total No. |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | Passengers & Cargo | Training | | Owned (purchased) | Leased | | | |
| | | | | | | | WL | DL | | |
| 1 | C-208 | ET-AVW | ✓ | | 12 | | | √ | 2014 | |
| **Total Sum** | | | **1** | | | | | 1 | | 1 |

## Amibara General Aviation Services

| No. | Aircraft Type | Reg. Mark | Role of Aircraft for | | Capacity (size) | Property Type | | | Years of production | Total No. | Remark |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | Passengers & Cargo | Training | | Owned (purchased) | Leased WL | Leased DL | | | |
| 1 | TURBO-THR | ET-AHN | | | | √ | | | 1981 | | Spray Services |
| 2 | AG-CAT | ET-AMC | | | | √ | | | 2008 | | Spray Services |
| **Total Sum** | | | | | | 2 | | | | 2 | |

## East African Aviation

| No. | Aircraft Type | Reg. Mark | Role of Aircraft for | | Capacity (size) | Property Type | | | Years of production | Total No. | Remark |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | Passengers & Cargo | Training | | Owned (purchased) | Leased WL | Leased DL | | | |
| 1 | KING AIR B-300 | ET-ATF | ✓ | | 6 | √ | | | 1999 | | Recently 2 aircrafts have been sold to other new operator |
| **Total Sum** | | | 1 | | | 1 | | | | 1 | |

## Trans Nation Airways (TNA)

| No. | Aircraft Type | Reg. Mark | Role of Aircraft for | | Capacity (size) | Property Type | | | Years of production | Total No. |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | Passengers & Cargo | Training | | Owned (purchased) | Leased WL | Leased DL | | |
| 1 | DHC-8-200 | ET-AKZ | ✓ | | 37 | √ | | | 1998 | |
| **Total Sum** | | | 1 | | | 1 | | | | 2 |

## Zemen Airways

| No. | Aircraft Type | Reg. Mark | Role of Aircraft for | | Capacity (size) | Property Type | | | Years of production | Total No. |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | Passengers & Cargo | Training | | Owned (purchased) | Leased WL | Leased DL | | |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | A5350B3 | ET-AKZ | ✓ | | 50 seats | | | √ | 1992 | |
| 2 | | | | | 5 seats | | | √ | | |
| **Total Sum** | | | | | | | | **2** | | **2** |

**Data Source:** Air worthiness Dir. Operator Certification Surveillance Dir. and Private Operators

**Form-1**

Operator's Name -------------------------------------------------------------------------------------

### 1. Aircraft Data

| No | Air Craft Type | Registration Mark | Role of Aircraft For | | | Capacity (Size passengers) | Property Type | | | Years of Production | Retired Date | Total No |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | Owned (purcha sed) | Leased | | | | |
| | | | Passengers | cargo | Training | | | WL | DL | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |

Average
- * Purchased Aircraft cost $ ---------------------------------
- * leased Aircraft cost: WL-wet-leasing -------------------- DL -Dry leasing $ ----------------------

**Form -2**

Operator's Name ----------------------------------------------------------------------------------------

**2. Human Resource Data**

| No | Name of employee | Position | Sex | | Educational level | | | | Field of study | | Years of Experience |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | F | M | Above degree | Degree | Diploma | Certificate | Aviation Field | Non-Aviation Field | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| Total | | | | | | | | | | | |

**Form -3**

Operator's Name ---------------------------------------------------------------------------------

**3. Passengers Data**

| No | Aircraft type | Purpose of flight | No of passengers (Embarked) | No of passengers (Disembarked) | Total no of Passengers | No of passengers, (Year -----------E.C) First Quarter | Second Quarter | Third Quarter | Fourth Quarter | Total Yearly passengers | Charge per passenger (USD/ BIRR) | % Charge (based on the previous year) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6= (4+5) | 7 | 8 | 9 | 10 | 11= (7+8+9+10) | 12 | 14 |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| Total | | | | | | | | | | | | |

Form -4

Operator's Name -----------------------------------------------------------------------------------

**4. All Cargo Data**

| No | Aircraft type | Cargo Load Origin/ Airport Name/ | Cargo Load Destination /Airport Name- | Total no of Passengers | No of passengers, (Year -----------E.C) | | | | Total Cargo Load Yearly (in Kg) | Charge per Kg (USD/ BIRR) | % Charge (based on the previous year) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | First Quarter | Second Quarter | Third Quarter | Fourth Quarter | | | |
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5= (3+4) | 6 | 7 | 8 | 9 | 10= (6+7+8+9) | 12 | 14 |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| Total | | | | | | | | | | | |

Form -5

Operator's Name ----------------------------------------------------------------------------------

**5. Aviation Training Data**

| No | Type of Training | Level of Training | | | | No of students Year ----------------------(E.C) | | | | | Remark |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | Master | Degree | Diploma | Certificate | First Quarter | Second Quarter | Third Quarter | Fourth Quarter | Total no of students | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| Total | | | | | | | | | | | |

Form -6

Operator's Name --------------------------------------------------------------------------------

**6. Finance Status Data (Income/Expenditure)**

| | | Income /Expenditure | | | | | | | | | | | | | | | | Remark |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| No | **Type of Income** | Sept | Oct | Nov | 1st quarter | Dec | Jan | Feb | 2nd quarter | Mar | May | Apr | 3rd quarter | Jun | Jul | Aug | 4th quarter | |
| 1 | Passengers Transportation | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2 | Cargo Transportation | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3 | Aviation Training | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4 | Others | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| **Total** | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| No | **Type of Expenditure** | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | Salary | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2 | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3 | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4 | Others | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| **Total** | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

**The Form is filled by-----------------------------------------------------**

**Approved by-------------------------------------------------**

**Sign----------------------------------------------------**

**Sign----------------------------------------------------**

**Date-----------------------------------------------------**

**Date------------------------------------------------------**

**7. Bank Financial Statement**

## 1. የግል ኦፕሬተሮች በኢትዮጵያ

የአቪዬሽን ኢንዱስትሪ በሀገራችን የተጀመረው ከሰባት አስረተ ዓመታት በፊት ሲሆን፣ በተለይ ከጣላይን ወራራ በፊት ተጀምሮ የነበረው እንቅስቃሴ በወራራው ምክንያት ተዳክሞ ቆይቷል፡፡ የጣላይን ወራሪው ተሸንፎ ከሀገራችን ከተባረራ በኋላ ኢንዱስትሪው እንዲያንሰራራ በማድረግ፣ ዘርፉ አለም አቀፍ አሰራር እንዲከተል እንዲያስችል በ1937 ዓ/ም የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን መስርያ ቤት የዛሬው የሲቪል አቪዬን ባለሥልጣን እንዲቋቋም ተደረገ፡፡

እ.ኤ.አ በ1944 የአለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት (International Civil Aviation Organization) ለማቋቋም ጥሪ ከተላለፈላቸው ሀገራት አገራችን አንዷ በመሆን ስብሰባው ላይ ለመሳተፍ ችላለች፡፡ የስብሰባው ዓላማም የአለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ለማሳደግ፣ በሀገራት መሀከል መግባባት እና ወዳጅነት ጸንቶ እንዲቆይ እንዲሁም በአቪዬሽን ኢንዱስትሪው የሚደርሱ የደህንነት ስጋቶች በጋራ ለመከላከል ነበር፡፡ በስብሰባው ማብቂያ የኮንቬንሽኑ (Convention on International Civil Aviation) ሰነድ ላይ ፈራሚ በመሆን በቀጣዩ ዓመት ድርጅቱ በይፋ ሲመሰረት አገራችን ከመስራች አገሮች አንዷ ሆናለች፡፡

ከዚህ በኋላ ነበር በአገራችን ቀደም ሲል የተጀመረው የአቪይሽን ዘርፉ ይበልጥ እንዲጎለብት፣ አለም አቃፋዊ ይዘት እና አሰራር እንዲከተል የተደረገው፡፡ በአቪዬሽን ዘርፍ ያሉት ተቋማት የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ጨምሮ የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት አሁን የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች እንዲሁም የኢትዮጵያ አየር መንገድ በተለያዩ ዓመታት የተለያዩ ስያሜዎች እና አደረጃጀት በመያዝ አለማቀፋዊ ይዘት እንዲኖራቸው አቅማቸውን በማሳደግ አሁን ላሉበት ደረጃ ደርሰዋል፡፡

የኢትዮጵያ አየር መንገድ አለም አቀፋዊ ሥራውን ሲጀምር እ.ኤ.አ በኤፕሪል/2046 አለምአቀፍ በረራው ከአዲስ አበባ ካይሮ C-47 ዶግላስ አይሮፕላን በመጀመር፤ ላለፉት ሰባት ዓስርተ ዓመታት አቅሙን በሰው ኃይል ፣ በመሰረተ ልማት፣ በየጊዜው በሚፈበረኩ ዘመናዊ አይሮፕላኖችን ባለቤት በመሆን እና በመከራየት፣ ወቅቱ በሚጠይቀው ቴክኖሎጂ እና በስልጠና አቅሙን በማሳደግ እንዲሁም አለም አቀፍ የበረራ መዳረሻዎችን በማስፋት በአፍሪካ እና አለም አቀፍ ደረጃ እውቅናን ካተረፉት አየር መንገዶች ረድፍ እንዲቀመጥ አድርጎታል፡፡

ብሄራዊ አየር መንገዱ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ከፍተኛ የመንግስት ድጋፍ አልተለየውም፡፡ አገሪቱ በብዙ መልኩ የምትከተለው የእዝ የኢኮኖሚ ስርዓት ስለነበረ በግል ለሚቋቃሙ የግል ኢንዱስትሪዎች ለመመስረት እድሉ አልነበረም፡፡ የኢህአዴግ መንግስት አገሪቱን ማስተዳደር ከጀመረ ጀምሮ ነጻ የኢኮኖሚ ስርዓት ቢመሰረትም በልማታዊ መንግስት አስተሳሰብ ስለሚመራ ለብሄራዊ አየር መንገዱ ለረጅም ለዓመታት በሞኖፖል ወይም በተቀራረበ ሞኖፖሊ(near monopoly) በሚመስል ሁኔታ ትኩረት እና ድጋፍ እየተሰጠው ቆይቷል፡፡ በመሆኑም የግል የአየር ትራንስፖርት ኦፕሬተሮች ታሪካዊ አመሰራረት በጣም አጭር ጊዜ ነው ፡፡

ከ15 ዓመታት ወዲህ መንግስት የግል ባለኃብቱ በተለያዩ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ኢንቨስት እንዲያደርግ በማሰብ የአገሪቱን የኢኮኖሚ ልማት በማፋጠን፣ የህዝቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል በማሰብ የአቪዬሽን ኢንዱስትሪውም ትኩረት እንዲያገኝ ተደርጓል፡፡

በዚሁ መሰረት የጠቅላላ የአቪዬሽን አገልግሎት የኢንዱስትሪው አካል አንዱ በመሆኑ፣ ዘርፉ እንዲስፋፋ በማድረግ፣ ጤናማ የሆነ ተወዳዳሪነትን በማስፈን ተጠቃሚው የተለያዩ አማራጮች እንዲኖረው እንዲሁም ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዲኖረው በማሰብ በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 ከ50 መቀመጫዎች ያለበለጡ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን ባለሃብቶች በንግድ ሥራው እንዲሳተፉ በአዋጅ ተፈቀደ፡፡

የአዋጁን መውጣት ተከትሎ ከ30 በላይ የግል ባለኃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ አውጥተው መንቀሳቀስ ጀምረው ነበር፡፡ ሆኖም ግን ካንፓኒውን ለማቋቋም እንዲሁም የንግድ ሥራው ለማስኬድ ከፍተኛ የካፒታል ወጪ (the high capital costs of establishing and running airlines) ስለሚጠይቅ፣ ለዘረፍ በልዩ ሁኔታ የሰለጠነ የሰው ኃይል ገብያ ላይ በስፋት ለማግኝት አዳጋች በመሆኑ እና በሌሎች በራሳቸው ምክንያት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከወሰዱት ውስጥ ተመናምነው በአሁኑ ወቅት እስከ 8 የሚደርሱ ኦፕሬሮች ይገኛሉ፡፡ እነዚህም አቢሲኒያ የበረራ አገልግሎት ፣ትራንስ ኔሽን ኤይርዌይስ፣ አኳሪየስ አቪዬሽን፣ ናሽናል ኤይርዌይስ፣ዘመን የበረራ አገልግሎት፣ኢስት አፍሪካ አቪዬሽን፣ ዋሊያ ኤርዌይስ፣ አሚባራ የእርሻ ልማት ድርጅት ናቸው፡፡

እነዚህ የግል ኦፕሬተሮች በአብዛኛው የቻርተር ፣ የአንቡላንስ ፣ የጭነት እና የርጭት አገልግሎት መደበኛ ያልሆኑ በረራዎች በሀገር ውስጥ እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ ከጥቂት ወራት ወዲህ ጥቂቶቹ መደበኛ የበረራ አገልግሎት በአገር ውስጥ እና በጎረቤት አገራት በመስጠት ላይ የሚገኙ ሲሆን፣ የተወሰኑ የግል ኦፕሬተሮች ከበረራ አገልግሎት በተጨማሪ የአቪዬሽን ስልጠናዎችን በመስጠት ሥራ ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ፡፡

## 2. የግል ኦፕሬተሮች ያሉበት ነባራዊ ሁኔታ

### 2.1 ዓለማቀፋዊ፣ አሁጉራዊ እና አገራዊ ሁኔታ

በዓለም አቀፍ ደረጃ የአየር ትራንስፖርት በርቀት ላይ የሚኖሩ ሰዎችን ለማጓጓዝ የሚያገለግል አንዱ የትራንስፖርት መሳሪያ በመሆኑ የህብረተሰብ ትስስርን ከመፍጠርና በተለያዩ አካባቢዎች የሚኖሩ ማህበረሰቦችን ከማገናኘት አኳያ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ አገራት ለሚያደርጉት የንግድ ልውውጥ፣ በቱሪዝም፣ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በርካታ የሥራ እድሎችን በመፍጠር፣ የኑሮ ደረጃን በማሻሻል፣ ድህነትን በመቀረፍና የውጭ ምንዛሪን ገቢ ምንጭን በማሳደግ ዓይነተኛ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል፡፡ ዘርፉ ቀጣይነት ላለው የኢኮኖሚዊና ማህበራዊ እድገት ዋነኛ ቁልፍ የትርንስፖርት መሰረተ ልማት ሆኖ እየገለገለ ይገኛል፡፡

የአየር ትራንስፖርት በአገሮች ኢኮኖሚ እና ፖለቲካዊ ሁኔታ ሳይወሰን ከአገር ውስጥ ባሻገር ድንበር ተሻጋሪ በመሆኑ አንድ ወጥ በሆነ ደረጃና አሰራር የሚመራ ዘርፍ ነው፡፡ ለዚህ ወጥ አሰራር የዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት (International Civil Aviation Organization) ያወጣቸውን ሳታንዳርዶች፣ አሰራሮች፣ በተለያዩ ጊዚያት እየተሻሻሉ በሚወጡ 19ኙ ተቀጽላዎች (annexes) በኮንቬንሽኑ ሰነድ (The Convention on International Civil Aviation) አገራት በመውሰድ በዚህ መርህ ተከትለው ይሰራሉ፡፡

የዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ሲቋቋም በመርህ ደረጃ ከሚከተላቸው ስምምነቶች አንዱ ፈጣንና ቀልጣፋ የአቪዬሽን አገልግሎት ማረጋገጥ የአቪዬሽን ኢንዱስትሪ ከማንኛውም ህገወጥ ጣልቃ ገብነትና ድርጊቶች መከላከልን ነው፡፡ የአቪዬሽነ ኢንዱስትሪው ደህንነቱ የተጠበቀ ፣ ቀልጣፋ፣ ቀጣይነት ያለውና ከአደጋ ስጋት የነጻ የአየር ትራንስፖርት በዓለም እንዲያድግ አንድ ወጥ የሆኑ ደረጃዎችንና ተመራጭ አሰራሮችን በመመስረት አገራት እንዱስትሪው ከደረሰበት የቴክኖሎጂ እድገት ደረጃ የተጣጠመ አገልግሎት ለመስጠት እንዲችሉ የየራሳቸው የተጣጠመ ደንቦች እና መመሪያዎችንም ለማዘጋጀት እገዛ አድርጓል፡፡
አባል አገራት ከድርጅቱ መርሆዎች እና አሰራሮች በማይጣረስ ሁኔታ ስታንዳርዶች፣ አሰራሮች ፖሊሲዎች እና የውስጥ መመሪያዎች ከሀገራቸው ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣም የተለያዩ ደንቦች ፣የውስጥ መመሪያዎችን በማዘጋጀት ደህንነቱ የተጠበቀ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት በሀገር ውስጥ እንዲስፋፋ በማድረግ፣ አየር መንገዶቻቸው የአገልግሎት መደራሻቸውን በማስፋት ከሀገር አልፊው ወደ ሌላ አገራት የአየር አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡

ዛሬ በአለማችን አንድ አንድ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት እስከ 50001 የሚጠጉ በICAO ኮድ የተደረጉ የኮሜርሻል አየር መንገዶች አሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ በአብዛኛዎቹ በግል ካንፓኒዎች የተያዙ ሲሆኑ ቀሪዎቹ በመንግስት የሚተዳደሩ ናቸው፡፡

በመንግስት ከተያዙትም ውስጥ በአንድ አንድ አገራት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በግል ካንፓኒዎች የአክሲዮን ድርሻ ባለቤትነት የተያዙ ናቸው፡፡ ለምሳሌ የጀርመኑ ሉፍታንዛ፣ የእንግሊዙ የብሪቲሽ ኤይር ዌይስ፣ የጃፓኑ ጃፓን ኤይር ላይን እንዲሁም አብዛኛዎቹ ዩኤስ ኤ አየር መንገዶች የመሳሰሉት የየሀገራቸው ተወካይ አየር መንገዶች ቢሆንም በግል ካንፓኒ የሚተዳደሩ ናቸው፡፡

በሌሎች አገራት ለምሳሌ የፈረንሳዩ ኤይር ፍራንስ ፣ በጣሊያን አሊታሊያ ፣ የራሽያው ኤይርፊሎት፣ የሳውዲ አየር መንገድ ሳውዲያ ፣ የኬኒያው ኬኒያ ኤይርዌይስ፣ የኔዘርላንዱ ኬኤልኤም(KLM) በከፊል መንግስት እና በግል ካንፓኒዎች አክስዮን ድረሻ በለቤትነት የሚተዳደሩ ናቸው፡፡

በአፍሪካ አገራት ከተወሰኑት በስተቀር ይህ ነው የሚባል ጠንካራ ብሄራዊ አየር መንገድ ሳይኖራቸው ወይም ብሄራዊ አየር መንገዶቻቸው በተደካሙበት ሁኔታ የሀገር ውስጥ በረራቸው በግል ካንፓኒዎች በተቋቋሙ የንግድ አየር መንገዶች አገልግሎቱን እየተሰጠ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ የቅርብ ጎረቤቶቻችን ኬኒያ ካላት ከብሄራዊ አየር መንገዷ (Kenya Airways) በተጨማሪ እንደ Aero-Pioneer Group, Jambojet የመሳሰሉ እና ሌሎች ከ30 በላይ በግል የተቋቋሙ ኦፕሬተሮች አሉ፡፡ በተመሳሳይ በታንዛኒያ Auric Air, Fastjet Tanzania, ከ16 በላይ በግል የተቋቋሙ ኦፕሬተሮች፣ በደቡብ አፍሪካ ከብሄራዊ አየር መንገዱ South African Airways በተጨማሪ Kululan , South African Express, ከ20 በላይ የግል ኦፕሬተሮች፣ ግብጽ ከብሄራዊ አየር መንገዱ Egypt Air በተጨማሪ Air Cairo, Air Sinai ከ18 በላይ የግል ኦፕሬተሮች እንዲሁም በናይጄሪያ ከ16 በላይ የግል ኦፕሬተሮች የመደበኛና መደበኛ ያልሆኑ የበረራ አገልግሎቶች ይሰጣሉ፡፡

[1]There is only one list of airlines arranged by owner and it lists airlines that are owned by the government of a country. There are over 5000 airlines with ICAO codes. The world's largest airline by fleet size and passengers carried is AmericanAirlines, operating from the United States. (https://www.aviationfanatic.com/ent_list.php?ent=9)

ስለሆነም በግል ካንፓኒዎች የሚቋቋሙ አየር መንገዶች አሀገር ውስጥ እና በአገራት መካከል በሚደረጉ የሰዎች እንቅስቃሴ፣ ለሚያደርጉት የንግድ ልውውጥ፣ በቱሪዝም፣ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በርካታ የሥራ እድሎችን በመፍጠር እንዲሁም የውጭ ምንዛሪ የገቢ ምንጭን በማሳደግ ለዘረፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊ እድገት አስተዋጾ በማድረግ ከፍተኛ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛሉ፡፡

2.2 የግል ኦፕሬተሮች ያሉበት ሀገራዊ ሁኔታ

የአቪዬሽን ኢንዱስትሪ በኢትዮጵያ መንግስት ለዘርፉ እድገት በሰጠው ትኩረት እና አንድአንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከ20 በመቶ በላይ የእድገት ምጣኔ እያሳየ ይገኛል፡፡

ለኢንዱስትሪው እድገት ከፍተኛውን ድርሻ የሚወስደው የኢትዮጵያ አየር መንገድን የሀገሪቱ በሄራዊ አየርመንገድ (flagship National carrier) በመሆን ላለፉት ሰባት አስርተ ዓመታት በሁሉም መልኩ ከፍተኛ ልምድ በማካበት በአፍሪካ እና በሌሎች ሀገራት ባሉት መደረሻዎች በሚሰጠው ቀልጣፋ የበረራ አገልግሎት በአፍሪካ ስመጥር እና የመጀመሪያው አየር መንገድ ለመሆን በቅቷል፡፡

የአየርመንገዱ ቀጣይነት ያለው እድገት እና ትርፋማነት ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉት በጥሩ አለምአቀፋዊ የካንባኒ ማኔጅመንት አሰራር በመመራቱ፣ አለማቀፍ አሰራሮችን ስታንዳርድ እና መርሆዎች ተከትሎ የሚሰራ እንዲሁም በተቆጣጣሪው ባለሥልጣኑ በተቀመጡ ስትንዳርዶች እና አሰራሮች ቁጥጥር የሚደረግበት በመሆኑ ነው፡፡

ከዚሁ በተጨማሪ አሁንም ሆነ ቀደምት የነበሩት የሀገሪቱ መንግስታት ለብሄራዊ አየር መንግዱ ከፍተኛ ትኩረት እና ድጋፍ በማድረጋቸው ፣ መንግስት ጣልቃ ሳይገባ እራሱ በራሱ ሊያስተዳደር የሚችልበት (Self Autonomy) ቁመና ተስጥቶ እየሰራ በመገኘቱ ዛሬ በሀገሪቱ ብሎም ከአፍሪካ ካሉት ጥቂት የኮርፐሬት ድርጅቶች የመጀመሪያው ተርታ እንዲቀመጥ አድርጎታል፡፡

ይህ በመሆኑ ነው ዛሬ በአለም ላይ 120 መዳረሻዎች ያሉት አየር መንገዱ፣ ለደንበኞቹ በአገልግሎቱና በደህንነቱ በሚሰጠው አገልግሎት  በቅርብ ጊዜ በፈረንሳይ ፓሪስ በተከናወነ የስካይተራክስ 2019 አለማቀፍ የአየር መንገዶች ሽልማት ከአፍሪካ "ምርጥ አየር መንገድ" በመባል ለ3 ተከታታይ አመታት ከአፍሪካ የአንደኛነት ደረጃውን አስጠብቆ ቆይቷል፡፡ በተጨማሪም አየር መንገዱ ከአፍሪካ አየር መንገዶች ምርጥ "የቢዝነስ ክላስ" እና "ምርጥ የኢኮኖሚ ክላስ" አገልግሎት ባለቤት ነው ተብሏል፡፡ አየር መንገዱ አሁንም በአፍሪካ የመሪነቱን ቦታ ይዞ ለመቀጠል ተግቶ እየሰራ ይገኛል፡፡

በግል ድርጅቶች ተቋቁመው የሚካሄዱ የአቬዬሽን ኦፕሬሽን ሥራዎች እንደ ብሄራዊ አየር መንገዱ በጠንካራ መሰረት ላይ የተቀመጡ አይደሉም፡፡ መንግስት በተከተለው የነጻ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ስርዓት ቀስ በቀስ  ከ20 ዓመታት በፊት አንድ በማለት በግል የተቋቋሙ ሀገር በቀል ኦፕሬተሮች እንቅስቃሴ ተጀመረ፡፡ አቢሲኒያ የበረራ አገልግሎት በግል ከተቋቋሙት የመጀመሪያው ፈር ቀዳጅ እና እስካሁን ዘልቆ የቆየ የግል አየር መንገድ ድርጅት ነው፡፡

የንግድ ሥራ ፈቃድ አውጥተው ዘግይተው ወደ ኦፕሬሽን ሥራ ላይ የሚገኙት  የአቢሰኒያ የበረራ አገልግሎት በተጨማሪ  ፣ትራንስ ኔሽን ኤይርዌይስ፣ አኳሪየስ አቪዬሽን፣ ናሽናል ኤይርዌይስ፣ዘመን የበረራ አገልግሎት፣ኢስት አፍሪካ አቪዬሽን፣ዋሊያ ኤርዌይስ እንዲሁም አሚባራ የእርሻ ልማት ድርጅት ይገኙበታል፡፡ የግል ዘርፉ ከሌሎች አፍረካ አገራት ከጎረቤቶቻችን ከኬኒያ እና ከታንዛኒያ ካሉት አገራት ጋር እንኳን ሲነጻጸር ገና በአዝጋሚ እንቅስቃሴ ላይ የሚገኝ ዘርፍ ነው፡፡

የግል ዘርፉ  በመንግስት በኩል እንደ ብሄራዊ አየር መንገዱ የሚደረጉ ድጋፎች በቂ ነው ባይባልም በተለይ ኢንዱስትሪው ለማቋቋም እና ስራውን ለማስኬድ ከፍተኛ የሆነ መዋለ ንዋይ እና ድጋፍ እንዲሁም ከግል ኦፕሬተር ዘርፍ እንቅስቃሴ አንጻር ማነቆ የሆኑ ችግሮችን በመዳሰስ በተገኙ ጉድለቶች ላይ በመመስረት ሚወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች በሚፈለገው መጠን በቂ ባለመሆናቸው ነው፡፡

ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ በአዋጅ ከተሰጡት ሥልጣን ተግባርና ኃላፊነቶች አንዱና ዋናው ውስጥ የአቪዬሽን እንዱስትሪው በአገሪቱ እንዲስፋፋ ማድረግ ሲሆን በተለይ የግል ዘርፉ

በአየር አገልግሎትና ለጠቅላላ የአቪዬሽን አገልግሎት ለመሳተፍ የስራ ፈቃድ ከመስጠት ባሻገር ተያያዥ መመሪያዎችን በማዘጋጀት እና በሥራ ላይ በማዋል ቁጥጥር በማድረግ የግል የአቪዬሽን ዘርፉ የተፈለገው እድገት እንዲያስመዘግቡ መርዳት ይጠበቅበታል፡፡ ከዚሁ በተጨማሪ በተለይ በግል ኦፕሬተሮች ተዘውትረው የሚነሱ ለሥራዎቻቸው እንቅፋት የሆኑ ችግሮች በመለየት ለዘርፉ እድገት አፋጣኝ የሆኑ የመፍትሄ አቅጣጫዎች ሊቀመጡ ይገባል፡፡

### 3. የግል የአየር ኦፕሬተሮች ኢኮኖሚያዊ አስተዋጾኦ

አየር ትራንስፖርት እንደ አጠቃላይ ከሌሎቹ የትራንስፖርት መስኮች በተለየ ሁኔታ ፈጣን፣ አስተማማኝና ደህንነቱ የተጠበቀ አገልግሎት የሚሰጥ ከመሆኑም በላይ ገበያ በመፍጠር በማገናኘት፣ በሥራ ዕድል ፈጠራ፣ ቱሪዝምን በማስፋፋት፣ በወጪ ንግድ፣ ለአጠቃላይ ኢኮኖሚውና ለአካባቢ ጥበቃ ጉልህ የሆነ አስተዋጽኦ ያበረክታል። አቪዬሽን በተለይ በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች ፈጣን ኢኮኖሚያዊ እድገት በማምጣት በኩል ከፍተኛ አስተዋጾ ያደረጋል፡፡

ጥናቶች እንደሚያሳዩት እ.ኤ.አ ከ 1995 ጀምሮ የአለም ኢኮኖሚ እድገት (GDP) በ 2.8 በመቶ በየዓመቱ አድጓል፡፡ በዚህ ጊዜ የአለም የአየር ትራንስፖርት የመንገደኞች ቁጥር(Passengers air Traffic) 5 በመቶ እያደገ ነበር፡፡ በኢንዱስትሪው ሁኔታ ወደ 50 ሚሊዮን በአቪዬሽንና የቱሪዝም ሥራዎች ላይ እየሰራ ይገኛል፡፡ እንዲሁም እስከ 10 ሚሊዮን በቀጥታ በአየር ትራንስፖርት እንዲትሪው እየተሰተፉ ይገኛሉ፡፡ እንደ አለምአቀፍ የአየር ትራንስፖርት ምልከታ (Global Air Transport Outlook) የአለም አቀፍ የሲቪል አቪዬሽን ድርጅት(ICAO) እንደተነበየው ለሚቀጥሉት ዓመታት ቀጣይነት ያለው የትራንስፖርት እድገት እንደሚኖር እ.ኤ.አ በ2030 አሁን ካለበት የተሳፋሪ ቁጥር እስከ 6 ቢሊዬን እንደሚደርስ ይገመታል፡፡

እንደ ዓለማቀፉ የአየር ትራንስፖርት ጥናትና ምርምር ተቋም በቅርቡ ይፋ እንዳደረገው መረጃ መሰረት ደግሞ የአየር ትራንስፖርት በዓለማቀፍ ደረጃ ከ3 ቢሊዮን በላይ ተሳፋሪ፣ ከ40% በላይ በእሴት ደራጃ ያለ ወደ ውጭ የሚላኩ እቃዎች፣ ከ40% በላይ አለምአቀፍ ቱሪስቶች እንቅስቃሴ ከግማሽ በላይ የሚሆነው በአውሮፕላን የተጓጓዘ ነው፡፡ ዘርፉ እስከ ቅርብ ጊዜ ወዲህ 63 ሚሊዮን በላይ የሥራ ዕድሎችን የፈጠረ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ

በቀጥታና በተዘዋዋሪ በዓለም ኢኮኖሚ ላይ ከ2.7 ትሪሊዮን ዶላር ያላነሰ ድርሻ ያለውና ከጠቅላላ ዓመታዊ ምርት ከ3.5% በላይ የሚሸፍን ነው።

አየር ትራንስፖርት አገራዊ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በተመለከተ ለአገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛውን አስተዋጾ ከሚያደርጉ የኢንዱስትሪ ዘርፎች ውስጥ የሚመደብ ነው፡፡ የአቪዬሽን ዘርፍ በአገሪቱ በኢኮኖሚ እድገት(GDP contribution)፣ ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ባልሆኑ የስራ እድል ፈጣራዎች እንዲሁም በውጭ ምንዛሪ ግኝት ምንጭ ከፍተኛ አስተዋጾ እያደረገ ይገኛል፡፡

ከሁለት ዓመት በፊት በተደረገ የዳሰሳ ጥናት እንደሚያሳየው ባለፉት አስር ዓመታት የአቪዬሽን ዘርፉ ለአገሪቱ አጠቃላይ ኢኮኖሚ እስከ 10 በመቶ የሚሆን አስተዋጾ አድርጓል፡፡ ከ20 ሺህ በላይ ቀጥተኛ ቋሚ የስራ እድሎችን ፈጥሯል፡፡ የውጭ ምንዛሪ ግኝት በተመለከተም በተለይ ትልቁን የአንበሳውን ድርሻ የሚወስደው በብሄራዊ አየር መንገዱ ሲሆን፣ በመደበኛ የውጭ ሀገር የመንገደኞች እና የጭነት የበረራ አገልግሎት፣ በቱሪስት ጉብኝት እና በሌሎች ጠቅላላ የአቪዬሽን አገልግሎቶች ባለፉት 10 ዓመታት በብዙ ሚሊዬን ዶላር የውጭ ምንዛሪ  አስገኝቷል ፡፡

በጥናት ባይደገፉም አቪዬሽን ኢንዱስትሪው ቀጥተኛ ባልሆኑ የስራ እድሎች በመፍጠር በኩል የአየር ትራንስፖርት ከፍተኛ አስተዋጾዎ እያደረገ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ በጠቅላላ አቪዬሽን አገልግሎቶች በሚሰጥባቸው አካባቢዎች በግል ድርጅቶች የሚሰጡ የትራንስፖርት አገልግሎቶች፣በሆቴሎች፣ የጉዞ አስጎብኝ ድርጅቶች፣ የቱሪስት መዳረሻዎች ፣ በተለያዩ የስጦት እቃ መሸጫዎች ተዘማጅ በሆኑ የስራ ዘርፎች የሚደረጉ የቢዝነስ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በቀጥታም ባይሆን የተፈጠሩ የስራ እድሎች  ትልቁን ድርሻ በአቪዬሽን ዘርፉ የተገኙ  ናቸው፡፡

የግል ኦፕሬተሮች ከተቋቋሙበት ጊዜ ጀምሮ በቂ ባይሆንም በስራ እድል ፈጠራ፣ በውጭ ምንዛሪ ግኝት የራሳቸው አስተዋጾ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ በቅርብ ጊዜ በስራ ላይ ካሉት የግል ኦፕሬተሮች በሰበሰብነው መረጃ መሰረት ድርጅቶቹ ተቋቁመው ሥራ ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ ከሚያስገቡት ገቢ  ለመንግስት ከፍተኛ ግብር እየከፈሉ ይገኛሉ፡፡ ከ240 ዜጎች በላይ ቀጥተኛ የስራ እድል ፈጥረዋል፡፡

የግል ኦፕሬተሮች ባለፉት አምስት ዓመታት ለ68196 መንገደኞች የቻርተር በራራዎች፣ የአንቡላንስ እና የመደበኛ የበረራ አገልግሎት ሰጥተዋል፡፡ ከዚሁ በተጨማሪ 932260 ኪ.ግ የካርጎ የበረራ አገልግሎት ሰጥተዋል፡፡ ከነዚህ አገልግሎት በሚገኝ ገቢ ለመንግስት ግብር በመክፈል እንዲሁም በመጠኑም ቢሆን የውጭ ምንዛሪ ገቢ ግኝት በመፍጠር የራሳቸውን አስተዋጾ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡

## 4. 4. የአየር ትራንስፖርት የኢኮኖሚ ሬጉሌሽን በፋይናንስ እይታ

የኢኮኖሚ ቁጥጥር ማለት መንግስት ያስቀመጣቸውን የኢኮኖሚ ግቦች ለማሳካት የግል ዘርፉ ፈቃድ ወስዶ ሥራውን ሲያከናውን እንዲያሟሉ የሚፈልገውን መስፈርቶች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ ተቆጣጣሪ አካል በህግ በተሰጠ ስልጣን መሰረት ህግን የተከተለ ቁጥጥር ማድረግ ነው፡ በሌላ አነጋገር በግብይት ሂደት የሚፈጠሩ የገበያ ጉድለት፣ አካባቢ ከብክለት ለመከላከል፣ በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ የሚኖሩ አሻጥሮች ለመቆጣጠር በልዩ ልዩ የንግድ እና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ላይ በተሰማሩ ድርጅቶችና ግልሰቦች ላይ እነዚህን ችግሮች ለከመከላከል የወጡ ህጎችንና መመሪያዎች ኃላፊነት በተሰጠው የመንግስት አካል ተፈጻሚ ማድረግ ነው፡፡

በመሰረቱ በግል የተሰማሩ ድርጅቶች በአብዛኛው ዓላማ አርገው የሚንቀሳቀሱት ትርፍን ማሳደግ ሲሆን ፣በዚህ ሂደት በእነዚህ አገልግሎት ሰጪዎች እና አገልግሎቱን ለማግኘት ከሚፈልጉ ተጠቃሚዎች (መንግስትና ህዝብ) ጋር የጥቅም ግጭት ይከሰታል፡፡ እነዚህ ያለመስማማቶች ሲከሰቱ ቁጥጥር በማድረግ ወደ መስመር ሊገቡ የሚችልበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ የኢኮኖሚ ቁጥጥር የሚደረገው በግል በተሰማሩ ድርጅቶች ከህዝብ ጋር ወይም ከመንግስት ጋር በሚፈጠሩት የጥቅም ግጭት ብቻ ሳይሆን በግል ድርጅቶች መሀከል አንዱ ድርጅት ከአሰራር ውጪ በሌላው የግል ድርጅት ላይ ህግን ባልተከተለ ሁኔታ እና እኩል የውድድር መንፈስ ያልተላበሰበት ሁኔታ ሲከሰት በተቀመጡት ህጎች መሰረት ተቆጣጣሪው አካል ጣልቃ በመግባት ችግሮቹ እንዲስተካከሉ ያደርጋል፡፡

በአጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ ቁጥጥር በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ቁጥጥር የሚደረግባቸው አካላት የሚያከናውኑት የንግድ ሥራ ተስፋ ለማስቆረጥ ሳይሆን ህጉ በሚፈቅደው ሁኔታ ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ ወደ ትክክለኛው መስመር እንዲገቡ ለማስቻል የሚወጣ የመንግስት የህግ ማእቀፍ ነው፡፡

### 4.1 የአየር የኦፕሬተሮች የኢኮኖሚ ቁጥጥር አግባቦች ተሞክሮ

የአየር ትራንስፖርት የኢኮኖሚ ቁጥጥር ሂደት የሚፈጸመው በአገራት የሚገኙ የሲቪል አቪዬሽን ተቋማት በተሰጣቸው ስልጣንና ኃላፊነት በመመስረት የዓለማቀፉ የሲቪል አቪዬሽን ድርጅት International Civil Aviation Organization (ICAO)፣ ያወጣቸውን ህጎች እና የተቀመጡት ስትንዳርዶች እና አሰራሮች ባልተጣረሰ ሁኔታ ከየሀገራቸው ተጨባጭ ሁኔታ በመንተራስ መመሪያዎችን በማውጣት በአገር በቀል እና በውጭ አየር መንገዶች ላይ ጠንከር ያለ አየር ትራንስፖርት ቁጥጥር ያደርገሉ፡፡

የየአገራት ልምድ ብንመለከት ናይጄሪያ ጠንካራ የብሄራዊ አየር መንገድ ባይኖራተም በአገሯ ውስጥ በሚበሩ አገር በቀል እና የውጭ አየር መንገዶች ላይ ጠንከር ያለ አየር ትራንስፖርት ኢኮኖሚ ሬጉሌሽን ህግ አላት፡፡ ህጉ በዋናነት ትኩረት የሚያደርገው በመደበኛ ፣ መደበኛ ላልሆኑ የንግድ አየር መንገዶች፣ በንግድ ስራ ባልተሰማሩ የግል አየር መንገድ፣ ወደ አገሯ በሚበሩ የውጭ አገር አየር መንገዶች ላይ የንግድ ላይሰንስ በመስጠት፣ እንዲሁም ጠቅላላ የአቪዬሽን አገልግሎት የሚሰጡ የፋስሊቴሽን፣ ኤሮድሮም ፣ የኤር ናቭጌሽን አገልግሎት የሚሰጡ የአገልግሎት ደረጃዎችን በማውጣት፣ የሰርትፍኬሽንና የቁጥጥር እንደሚደረግ ህጉ ይደነግጋል፡፡ ከዚሁ በተጨማሪ የሬጉሌሽን ህጉ በንግድ ስምምነት የሚነሱ ክፍያዎች፣ ከኢንሹራንስ ክፍያዎች መጠን እና ህጋዊነት (Insurance premium) ፣ የትኬት እና የታሪፍ ክፍያዎች ፣ የሲቪል አቪዬሽን ክፍያ እና የአየር ትራንስፖርት ስታትስቲክስ ፣ አገር በቀል አይር መንገዶች የፋይናንስ አቋሚቸው በተመከለከተ፣ ጸረ ውድድር ህጎች እንዲሁም የአየር ትራንስፖርት ተጠቃሚዎች ከለላ እንዴት ቁጥጥር እንደሚደርግባቸው እና ይህንን ሲተላለፉ እንዴት መቀጣት እንዳለባቸው በህጉ ተደንግገዋል፡፡

ወደ ጎረቤታችን ኬኒያ ብንሄድ ሬጉሌሽኑ ትከረት የሚያደርገው በኤሮኖቲካል መረጃ አገልግሎት፣ የንግድ አየር መንገድ ኦፐሬሽን፣ የአሬድሮም ፣ ለአቪዬሽን ስልጠና፣ ለተፈቀዱ ድርጅቶቸ፣ ላይሰንሲንግ እና ሰርተፍኬሽን ፣ ለአውሮፕላን ፣ ብቃት ፣ዜግነት

እና ምልክት፣ ከሽማቾች ጥበቃ ፣ ከቅጣት እና ክፍያዎች የሚነሱ ጉዳዬች ይመለከታል፡፡ በህጉ ከተዘረዘሩት ጉዳዮች ጋር የሚነሱ አፈጻጸሞች እና የሚነሱ አለመስማማቶችን ለመፍታት የኬኒያ ብሄራዊ ሲቪል አቪዬሽን አስተዳደር ይግባኝ ፍርድ ቤት (National Civil Aviation Administrative Review Tribunal) አቋቁማለች፡፡ ይህ ፍርድ ቤት የአቪዬሽን አገልግሎት በሚሰጡ ድርጅቶች እና በተቆጣጣሪው ባለሥልጣን የሚነሱ ከላይሰንስ፣ ከሰርተፍኬሽን፣ ከቅጣት እና ከእገዳ ጋር የሚነሱ አለመግባባቶችን ይመለከታል፡፡

በአገራችን ባለሥልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 23/2001 አንቀጽ 92(2) መሰረት መመሪያን የማውጣት በአዋጁ ላይ የተዘረዘሩት ተግብርና ኃላፊነቶች ስርዓቶችና ደረጃዎች የያዙ ተከታታይነት ያለው የኢኮኖሚ ቁጥጥር አይፈጸምም፡፡ በዋናነት ትኩረት ተደርጎ የሚሰራው የንግድ አየር መንገዶች፣ የኢንቨስትመነት የንግድ ላይሰንስ በመስጠት፣ እንዲሁም የሰርትፍኬሽንና የቁጥጥር ከማድረግ የዘለለ ስራ አይከናወንም፡፡ እነዚህን ስራ ለመስራት ወጥ የሆነ መመሪያም አልተዘጋጀም፡፡ በኢንዱስትሪው ተለዋዋጭ እና ውስብስብነት ባህሪ አንጻር  አላስፈላጊ የሆኑ ህገ ወጥ ድርጊቶችን የመፈጸማቸው እድል ሊከፍት ይችላል፡፡ አገር በቀል አየር መንገዶች በአገር ኢኮኖሚ ላይ የራሳቸውን አስተዋጸ የሚጫወቱት ሚና እንደተጠበቀ ሆኖ አሰራራቸው ግልጸኝነት ሊኖረው ይገባል፡፡

በዚህ መሰረት ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ከቴክኒክ ኢንስፔክሽን ባሻገር ተከታታይነት ያለው ኢኮኖሚያዊ ቁጥጥር በማድረግ ተገቢነት የሌላቸውን አሰራሮች በማስተካከል እንዲሁም የግል የአየር ትራንስፖርት ዘርፉ ሊያድግ የሚችልበት ሁኔታ ለማመቻቸት ሊከሰቱ ከሚችሉ ተገቢ ያልሆኑ አሰራሮች አስቀድሞ ለመከላከል፣ ባለሥልጣኑ በአዋጅ ከተሰጠው የሥልጣን ተግባራት በመነሳት  በስራ ላይ ያሉትን ህጎች እና አሰራሮች በመፈተሽ አገር በቀል አየር መንገዶች እያከናወኑ ያሉትን አፈጻጸም ለመከታተል የፋይናንስ መመሪያ ማዘጋጀት አለበት፡፡

ተያያዥ ቅጾች

የግል ኦፕሬተሮች የኤርክራፍት ፣ የሰው ኃይል ፣የመንገደኛ፣ የጭነት፣ የስልጠና፣ የፋይናንስ መረጃዎች ቀጥሎ ባሉት ቅጾች (1-6) ተያይዘዋል፡፡